# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁ. 219931

ሰኔ 28 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች ፡- አቶ ዮናስ ደስታ ጠበቃ ተስፋዬ ሙሊሳ ቀረቡ

ተጠሪ ፡- አቶ ነጋሽ ኃይሌ- አልቀረ ቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጠ፡፡

## ፍርድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ነው፡፡ የክርክሩን አመጣጥ ከስር ፍርድ ቤት የመዝገብ ግልባጭ እንደተረዳነው አመልካች የስር 1ኛ ተከሳሽ፣ ተጠሪ ከሳሽ ሆነው ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪ ያቀረቡት ክስ ከአመልካች ጋር በተደረገ በአደራ ማስቀመጥ ውል ከውጭ ሀገር ይዤ የገባሁትን 225,000.00 የአሜሪካን ዶላር በአደራ አስቀምጬ ገንዘቡን የመመለስ ውል ነሀሴ 23 ቀን 2012 ዓ/ም የተፈጸመ ቢሆንም በውሉ መሠረት ያልመለሱት ቀሪ ገንዘብ 126,000.00 ዶላር ወደዶላር ሂሳብ አካውንቴ እንዲያስገቡልኝ እንዲወሰን የሚል ሲሆን አመልካች ባቀረቡት መልስ ውሉ አሜሪካን ሀገር ስለተደረገ ፍርድ ቤቱ የመዳኘት ሥልጣን የለውም፤ ዶላሩን በአደራ የሰጠኝ አሜሪካን ሀገር ሲሆን ያለውን ቀሪ ገንዘብ 90,551.00 ዶላር አሜሪካን ሀገር መጥቶ መውሰድ ይችላል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤት ጉዳዩን መርምሮ ገንዘቡን በአደራ የማስቀመጥ ውሉ የተደረገው በኢትዮጵያ ቢሾፍቱ ከተማ በመሆኑ ፍርድ ቤቱ የመዳኘት ሥልጣን አለው፤ ነገር ግን የውጭ ሀገር ገንዘቡ ወደኢትዮጵያ ሲገባ ብሔራዊ ባንክ ባወጣው መመሪያ ቁጥር 49/2017 መሠረት ሕጋዊ ሥርዓቱን ጠብቆ ያልገባና የውጭ ሀገር ገንዘቡ በዚህ መጠን እና ለረጅም ጊዜ በግለሰብ እጅ እንዲቆይ የማይፈቅድ ስለሆነ በአደራ የማስቀመጥ ውሉ በፍ/ሕ/ቁ. 1716(1) መሠረት ሕገ-ወጥ ነው፤ ሕገ-ወጥ ውል የሚያስከትለው ሕጋዊ ውጤት የሌለ በመሆኑ ክሱ ተቀባይነት የለውም በማለት ወስኗል፡፡ ይግባኝ ሰሚ ችሎት በበኩሉ በፍ/ሕ/ቁ. 1716(1) መሠረት ሕገ-ወጥ ዓላማ ያለው ውል ነው የሚባለው የውሉ ግዴታ በራሱ ሕገ-ወጥ ሲሆን እንጂ ከውሉ በፊት የተፈጸመ ሕገ-ወጥ ተግባር መኖር አለመኖሩ መሠረት በማድረግ የሚወሰን አይደለም፡፡ ዶላር በአደራ ማስቀመጥን ሕገ-ወጥ የሚያደርግ የሕግ ድንጋጌ የለም፡፡ ዶላሩ በሕገ-ወጥ መንገድ ሀገር ውስጥ የገባ ነው ቢባልና ውሉ ፈራሽ ቢሆን እንኳን አመልካች ገንዘቡን የሚያስቀሩበትና ያላግባብ የሚበለጽጉበት ምንም የሕግ አግባብ የለም በማለት የሥር ፍርድ ቤትን ውሳኔ በመሻር በፍሬ ነገሩ አከራክሮ እንዲወሰን ጉዳዩን መልሷል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘትም ዶላርን በአደራ ማስቀመጥ በወንጀል ሕግ ቁጥር 346 እና የብሔራዊ ባንክን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 591/2000 አንቀጽ 26(4) መሠረት የወንጀል ድርጊት ሆኖ የተመለከተ ነው፡፡ ተግባሩ ወንጀል በመሆኑ ውሉ ሕገ-ወጥና ውጤት የሌለው ነው፡፡ በሕግ ወንጀል የተባለን ድርጊት በፍርድ ሕጋዊ ማድረግ አይቻልም፤ ውሳኔው መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው የሚል ሲሆን የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን ተመልክቶ ዶላር በአደራ ማስቀመጥ ውል ሕገ-ወጥ ተግባር አይደለም መባሉ ከመመሪያ ቁጥር 49/2017 እና ከፍ/ሕ/ቁ. 1716 አንጻር ተገቢነቱን ለመመርመር ተጠሪ መልስ እንዲያቀርቡ ያዘዘ ሲሆን ተጠሪ ያቀረቡት መልስ አመልካች በሥር ፍርድ ቤት ውሉ ሕገ-ወጥ ነው በማለት ያልተከራከሩ ስለሆነ በሥር ያልቀረበ ክርክር በዚህ ችሎት ሊያነሱ አይገባም፡፡ የውሉ ግዴታ ሕገ-ወጥ ሳይሆን ከውሉ በፊት የተፈጸመ ሕገ-ወጥ ተግባር መኖር አለመኖሩን የውሉን ዓላማ ሕገ-ወጥ አያደርገውም፡፡ የተከፈለው ገንዘብ ሳይመለስ ይቀራል ማለት የፍ/ሕ/ቁ. 1815 የሚቃረን እና አንደኛው ተዋዋይ ወገን ያላግባብ እንዲበልጽግ የሚያደርግ ነው፡፡ ውሳኔው ተገቢ ስለሆነ ሊጸና ይገባል ብለዋል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ በማቅረብ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም ተጠሪ ያቀረቡት ክስ የክስ ምክንያት ያለው መሆን አለመሆኑን? በጭብጥነት በመያዝ መዝገቡን መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው ተጠሪ ያቀረቡት ክስ ከአመልካች ጋር በተደረገ በአደራ ማስቀመጥ ውል ከውጭ ሀገር ይዤ የገባሁትን 225,000.00 የአሜሪካን ዶላር  በአደራ አስቀምጬ ገንዘቡን የመመለስ ውል ነሀሴ 23 ቀን 2012 ዓ/ም የተፈጸመ ቢሆንም በውሉ መሠረት ያልመለሱት ቀሪ ገንዘብ 126,000.00 ዶላር ወደዶላር ሂሳብ አካውንቴ እንዲያስገቡልኝ እንዲወሰን የሚል ነው፡፡ እንደሚታወቀዉ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

37/1 መሰረት ማንኛዉም ሰዉ አንድን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በሕግ የዳኝነት ሥልጣን ለተሰጠዉ አካል በማቅረብ ፍርድ ወይም ዉሳኔ(ፍትህ) የማግኘት መብቱን መጠቀም የሚችለዉና በተለይም ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤት ጉዳዩን ተቀብሎ አከራክሮ ዉሳኔ ወይም ፍርድ ሊሰጥ የሚችለዉ ዳኝነት የተጠየቀበት ጉዳይ በፍርድ ሊወሰን የሚገባ ጉዳይ (justiciable matter) ሆኖ ሲገኝ ብቻ ነዉ፡፡ ክርክሩን በፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ መሰረት መምራት እና መቆጣጠር የፍርድ ቤቱ ኃላፊነት ሲሆን በተገቢው ሁኔታ ካልተመራ የሥነ-ሥርዓት ሕጉን ዓላማዎች የሆኑትን እንደ እንጻራዊ እውነትን የመፈለግ፣ ሥነ-ሥርዓታዊ ፍትህ፣ ክርክርን ውጤታማ፣ ወጭና ጊዜ ቆጣቢ በሆነ አግባብ መምራት የመሳሰሉትን ማሳካት ስለማይቻል የተከራካሪዎችን መብት ይነካል፡፡ ፍርድ ቤት በራሱ አነሳሽነት ከሚመረምራቸው ጉዳዮች መካከል የመጀመሪያው በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 231(1)(ሀ) መሠረት በክስ አቤቱታው የተገለጸው የሚያስከስስ መሆን መሆን አለመሆኑን ነው፡፡ የክስ ምክንያት ከሕግ ወይም ከውል የመነጨ ግዴታ መኖሩን፣ የተጠየቀው ዳኝነት በፍርድ ቤት የሚዳኝ መሆን አለመሆኑን እና በክሱ ዝርዝር ውስጥ የተመለከቱት ጉዳዮች ቢረጋገጡ የተጠየቀውን ዳኝነት ለከሳሽ ለመወሰን ህግ የሚፈቅድ መሆን አለመሆኑን መመርመርን የሚጠይቅ ነው፡፡ ይህም የክስ ምክንያት የሌለው ጉዳይ የሚለው በዋነኛነት ዳኝነቱን ለመጠየቅ ከህግ የመነጨ ግንኙነት እያለው ግን በፍርድ ቤት ሊዳኙ የማይችሉ ጉዳችን (non-justiciable matters) ፍርድ ቤት አከራክሮ ሊፈጸም የሚችል ውሳኔ ሊሰጥባቸው የማይችሉ በመሆናቸውና ከሳሽ ወገን ክሱን ሲያቀርብ የጠቀሰው ወይም የገለጸው የክሱ መሰረት የሆነው ምክንያት በህግ የክስ መሰረት ሊሆን የማይችል ከሆነ የማያስከስስ ነው ተብሎ ክሱ ውደቅ የሚደረግበት ሥርዓት ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ የጠየቁት ዳኝነት ከአመልካች ጋር ያደረጉት ዶላር የማስቀመጥ የአደራ ውል መሠረት እንዲፈጸምላቸው ነው፡፡ ውል ሊመሠረት የሚገባው ሕጋዊ በሆነ ዓላማና ጉዳይ ላይ እንደሆነ በፍ/ሕ/ቁ. 1678(ለ) ላይ ተመልክቷል፡፡ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 346 ላይ የውጭ ሀገር ገንዘብን በአደራ ማስቀመጥ ወንጀል ሆኖ የተደነገገ ሲሆን በብሔራዊ ባንክ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 591/2000 አንቀጽ 26 በአዋጁ ሆነ በመመሪያ የተመለከቱ ግዴታዎችን መተላለፍ ወንጀል ስለመሆኑ ተቀምጧል፡፡ የብሔራዊ ባንክ መመሪያ ቁጥር ኤፍ.ኤክስ.ዲ. 49/2017 በክሱ የተመለከተውን መጠን ያሕል የውጭ ሀገር ገንዘብ መያዝ መከልከሉ የተመለከተ ስለሆነ ድርጊቱ በአዋጁ መሠረት ወንጀል ነው፡፡ ተዋዋዮች የመዋዋል ነጻነት ቢኖራቸውም በሕግ የተመለከተውን አሥገዳጅ ሁኔታ አልፈው መዋዋል አይችሉም፡፡ በዚህ ምክንያት ዶላር በአደራ ማስቀመጥ ውል ሕገ-ወጥ ተግባር በመሆኑ ፍርድ ቤቶች ሕገ-ወጥ ውልን ሊያስፈጽሙ አይችሉም፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 27739 (በቅጽ 06 እንደታተመ) ሕገ-ወጥ ውልን ለማስፈጸም የሚቀርብ ክስ፤ የክስ ምክንያት የሌለውና በፍርድ ቤት ሊስተናድ የማይችል ስለመሆኑ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ ስለሆነም ተጠሪ የዶላር አደራ ማስቀመጥ ውል እንዲፈጸምላቸው ያቀረቡት ክስ ሕገ-ወጥ ውል እንዲፈጸም ዳኝነት የተጠየቀበት ስለሆነ ጉዳዩ የክስ ምክንያት የለውም ብለናል፡፡ ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሉ ሕገ-ወጥ ውል አይደለም በሚል በሥረ-ነገሩ እንዲታይ መወሰኑ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

*ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

## ውሳኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 199289 ሕዳር 23 ቀን 2014 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡

2. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት መደበኛ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 317094 ጥቅምት 11 ቀን 2013 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ በውጤቱ ፀንቷል፡፡

3. ተጠሪ ባቀረቡት ክስ የጠየቁት ዳኝነት የክስ ምክንያት የለውም በማለት ወስነናል፡፡

4. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

## ትዕዛዝ

- የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡
- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

አ/ኃ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም